# የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም

# የደረጃ መለኪያ /ስታንዳርድ/

## (የተሻሻለ)

አ/አ/ትም/ቢሮ

ታህሳስ 2005 ዓ/ም

# ማ ው ጫ

ገጽ

መግቢያ ........ 1
1 የቅድመ - መደበኛ ትም/ፕሮግራም የደረጃ መለኪያ ........ 4
1.1 የቅድመ-መደበኛ ትም/ተቋማት አስፈላጊነት ........ 4
1.2 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ........ 5
1.3 የፕሮግራሙ አወቃቀር ........ 6
1.4 የፕርግራሙ አደረጃጀት ........ 6
1.4.1 ጨዋታ ........ 6
1.4.2 በክፍልና ከክፍል ውጭ ተቀናጅተው የሚሰጡ ፕሮግራሞች 6
1.4.3 ሥራ ........ 7
1.5 የፕሮግራሙ ወቅት /ካላንደር/ ........ 8
1.6 የክፍለ - ጊዜያት ሥርጭት ........ 9
1.6.1 ሳምንታዊ የክፍለ - ጊዜያት ሥርጭት ........ 9
1.6.2 ዕለታዊ ፕሮግራም መርሀ-ግብር ........ 10
1.7 የመምህራን የሥራ ሰዓት መጠን ........ 11
1.8 የማስተማር ዘዴዎች ........ 12
1.9 ከመምህራን የሚጠበቅ ባህርይ ........ 12
1.10 የቅድመ - መደበኛ መርሀ - ግብር ያጠናቀቁ ህፃናት ባህርይ ........ 13
1.11 የቅድመ - መደበኛ ትም/ ተቋማት የሚቋቋሙባቸው አካባቢዎች የህንፃው ሁኔታ ........ 13
1.11.1 የቦታ አመራረጥ ........ 13
1.11.2 የምድረ-ግቢው ገጽታና አደረጃጀት ........ 14
1.11.3 የቅድመ- መደበኛ ትም/ተቋማት መጠን ........ 14
1.11.4 የምድረ -ግቢና የህንፃዎች አደረጃጀት ........ 15
1.12 የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ተቋማት ሊኖሩት የሚገባ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ........ 16
1.13 ለልዩ ልዩ ክፍሎች አስፈለጊ መሣሪያዎች ........ 17
1.13.1 ለአንድ መማሪያ ክፍል የሚያስፈልጉ ቋሚ መሣሪያዎች.. 17

1.13.2 መስማት ለተሳናቸው ህፃናት ........................................ 17
1.13.3 ማየት ለተሳናቸው ህፃናት ........................................ 17
1.13.4 የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ላለባቸው ሕፃናት .................. 18
1.13.5 ለተግባራዊ ትምህርት የሚገለግሉ መሣሪያዎች ................ 18
1.13.6 የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ዕቃዎች ................ 18
1.13.7 ለመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች ........................................ 19
1.13.8 ለማዕድ ቤት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ................................ 19
1.13.9 አላቂ የመጫወቻ ዕቃዎች ................................................ 20
1.13.10 ቋሚ የውጭ መጫወቻ መሣሪያዎች .............................. 21
1.13.11 ለርዕሰ መምህር ቢሮ የሚያስፈለጉ ዕቃዎች .................. 21
1.14 የሰው ሃይል ምደባ ........................................................ 22
1.14.1 የመምህራንና የሠራተኞች ምደባ ...................................... 22
1.14.2 የመምህራንና የሠራተኞች ብዛት ...................................... 22
1.14.3 የመምህራንና የሠራተኞች የትምህርት ደረጃ ......................... 23
1.15 ልዩ ልዩ አስፈላጊ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት መመሪያዎች ..... 23
1.16 የቅድመ - መደበኛ ትም/ተቋም ከወላጆች፣ከህብረተሰቡና ከአመራር ጋር ሊኖረው የሚገባ ግንኙነት ........................................ 24
1.16.1 የወላጆች ሚና ............................................................ 24
1.16.2 የአመራር ሚና ............................................................ 25
1.16.3 የህብረተሰብ ሚና ........................................................ 25

## መግቢያ

የአንድ አገር የትምህርት ሥርዓት አደረጃጀት፣ የትምህርቱ አላማና ይዘት ህብረተሰቡ የደረሰበትንና ወደፊት ሊደርስበት የሚፈልገውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት ደረጃ ያንፀባርቃል።

የትምህርት ዓላማ ታዳጊው ትውልድ ሕብረተሰቡ ዘንድ ተፈላጊነት ያላቸውና በሥራ ሊተረጐሙ የሚችሉ ባህሪያትን/ዕውቀትን፣ ልዩ ልዩ ችሎታዎችን፣ ክህሎቶችን፣ ልምዶችን የተስተካከለ አመለካከትንና ወዘተ. እንዲጨብጥና በሕብረተሰቡ ሕይወት ንቁ ተሳታፊና አምራች ዜጋ እንዲሆን ማድረግ ነው። እነዚህ የተነደፉት የትምህርት ዓላማዎች በተግባር ሊተረጐሙ የሚችሉት ደግሞ አስፈላጊው ግብዓቶች በጥራት ተሟልተውና ተደራጅተው ሥራ ላይ ሲውሉ ነው።

በአገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የትምህርት ፕሮግራሞች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ያስፈልጋል። የአንድ አገር የትምህርት ጥራት ከሚገለጥባቸው ባህርያት መካከል ዋናዋናዎቹ፣

- የትምህርት ፖሊሲውና የትምህርት ዓላማው ግልጽነት፣
- በተማሪው ላይ ለማምጣት የተፈለገው የባህርይ ለውጥ በደረጃው ዓይነት፣ ግልጽነትና ስኬታማነት መለየት፣
- የሚፈለገውን ባህርይ ለማስገኘት የሚያስችል የትምህርት ይዘት ጥራትና ዓይነት፣
- የትምህርቱ አደረጃጀትና አወቃቀር አመቺነት፣
- የትምህርት መተግበሪያ ዘዴ፤ ስትራቴጂ በአጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርቱ ይገኙበታል። ከላይ የተጠቀሱት የባህርያት ጥራት፤ ብቃትና የምቹነት ደረጃዎች በአንፃራዊነት የሚታዩ፣ ደረጃ በደረጃ እያደጉና እየተለወጡ የሚሄዱ መሆናቸው ቢታወቅም፣ በአንድ በተወሰነ ወቅት መነሻቸውና የጥራት ደረጃቸው ተጠብቆ ስለመካሄዳቸው መመዘን መቻል አለባቸው።

አንድ የትምህርት ፕሮግራም ደረጃውን የጠበቀ ነው ለማለት የሚቻለው ዝቅተኛው /አነስተኛ/ መነሻ መለኪያ /እስታንዳርድ/ ተቀምጦለት በዛው መሠረት እየተጓዘ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

የአንድ አገር የትምህርት ጥራት ደረጃ ሊመዘን የሚችለው በአገሪቱ ውስጥ በሚኖረው የደረጃ መለኪያ /ስታንዳርድ/ አኳያ ሲገመገም፣ ተመሳሳይ ስታንዳርድ ካላቸው አገሮች አኳያ ተነፃፅሮ ሲታይና የተሻለ ስታንደርድ እየተጠቀሙ ነው ከሚባሉት አገሮች ጋር ሲገናዘብ ነው።

በአገራችን የትምህርት የዕድገት ደረጃ ሲታይ የተዘበራረቀ ከመሆኑም በላይ ፍላጐትንና አቅምን አጣጥሞ የሚራመድ አይደለም። ለምሳሌ ከአቅም በላይ እስከ 10,000 ተማሪዎች ይዘው የሚያስተናግዱ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ በአንፃሩ ደግሞ ከ400 እና ያነሰ ተማሪዎች ይዘው የሚጓዙ ትምህርት ቤቶች አሉ፤ በውስጥ ድርጅትና በበቂ የማስተማሪያ መሣሪያ የተደራጁና ያልተደራጁ አሉ። እንደዚሁም የመምህራን ብዛትና ጥራት፤ የመማሪያ ክፍሎች መጠን በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። በአንድ ክፍል ከ40-50 ተማሪዎች የሚማሩበትና በአንፃሩ ደግማ እስከ 90 የሚማሩበትም አሉ።

እነዚህና ሌሎች መሰል ችግሮች የትምህርቱ ዓላማ ግብ እንዳይመታ እንቅፋት ስለሚሆኑ ትምህርት ቤቶች በሥርዓተ ትምህርት፤ በትምህርት መሣሪያዎች፤ በመምህራን ችሎታና ብቃት በሕንፃቸው አደረጃጀትና በትምህርት አመራርና አስተዳደር ወዘተ. አጠቃቀም ተመጣጣኝና አስገዳጅነት ያለው መነሻ/መለኪያ/ስታንዳርድ/ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

ትምህርት ቤቶች በመንግሥትና በሕዝብ የጋራ ጥረት የሚመሩ፤ የሚተዳደሩና የትምህርቱ ዓላማ ግብ እንዲመታ የሚያበቁ ድርጅቶች ናቸው። በመሆኑም በትምህርት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች፤ በትምህርት ቤቶች ኢንቬስት የሚያደርጉ የግል ባለሀብቶች እንዲሁም በአጠቃላይ ህብረተሰቡ በየትምህርት እርከኑ ሊሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች ማወቅ ይኖርባቸዋል።

በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት አጠቃላይ ትምህርት በሚከተሉት እርከኖች ተደራጅቷል።

1/ የቅድመ - መደበኛ ትምህርት /2 ዓመት/

2/ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት /1-8/

ሀ. የመጀመሪያ ሳይክል ከ1-4 መሠረታዊ ትምህርት

ለ. ሁለተኛ ሳይክል ከ5-8 አጠቃላይ ትምህርት

3/ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት

ሀ. የመጀመሪያ ሳይክል /9-10ኛ/ የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠቃለያ

ለ. ሁለተኛ ሳይክል (11 - 12) ተማሪዎች በሕብረተሰብና በሳይንስ የትምህርት ዘርፎች ለከፍተኛ ትምህርት የሚዘጋጁበት የትምህርት እርከን ነው።

በትምህርቱ ዓላማ መሠረት በየእርከኑ የትምህርት ጥራት እንዲጠበቅና ወይም ስታንዳርዱን የተጠበቀ ለማድረግ መታየት የሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዩች፡-

- የትምህርቱ መዋቅር፤ የትምህርት ወቅትና የትምህርት ፕሮግራሞች፣
- የትምህርቱ ሥራ መመሪያዎች፣
- የትም/ቤቱ አደረጃጀት
  - የትምህርት ቤቱ ደረጃ
  - የሕንፃው ሥራ
  - የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ
  - የተማሪዎች ብዛት በትምህርት ደረጃና በእያንዳንዱ ክፍል
  - ልዩ ልዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎችና መሣሪያዎች
  - የመምህራንና፣ የሠራተኞች ብዛት፤ ዓይነትና የት/ደረጃ
  - መጻህፍት፤ የመምህሩ መምሪያና የተማሪዎች መማሪያ መጻህፍት
  - ለልዩ ትምህርት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፤ መጻሕፍት ወዘተ.. ሲሆኑ፤

እነዚህን የያዘ መነሻ የሚሆን የትምህርት ደረጃ መለኪያ/ስታንዳርድ/ ተሻሽሎና ተዘጋጅቶ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ስታንደርዱ የተዘጋጀው የትምህርቱን ሥራ በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ ነው። ይሁን እንጂ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን በአንድ ጊዜ ዕውን ለማድረግ ጊዜን የሚጠይቅ ስለሚሆን በተዘጋጀው ስትራቴጅና በወጣለት ዕቅድ መሠረት በአጭርና በረዥም ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል። በዚህ መሠረት የአጭር ጊዜው ዕቅድ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ ሁኔታዎች ማመቻቸት ሲሆን የረዥም ጊዜዕቅድ ደግሞ ስታንዳርዱን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ይሆናል። ይሁን እንጂ ትምህርት ቤቶችን በግል የሚከፍቱ ባለሀብቶች ስታንዳርዱን ጠብቀው እንዲሰሩ ይጠበቃል።

## 1) የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የደረጃ መለኪያ

### የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ተቋማት አስፈላጊነት

ሕፃናቱ ከዕድሜያቸው ለጋነት የተነሳ በማንኛውም ጊዜ ከየትኛውም የሕብረተሰብ ክፍል የበለጠ ለአደጋና ለጉዳት የተጋለጡ በመሆናቸው ልዩ ጥበቃ፣አያያዝና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው እሙን ነው። በተለይ በመጀመሪያዎቹ አምስት አመታት የሚደረግ እንክብካቤ ለህፃናት ህልውና ማለትም መኖር አለመኖር እንዲሁም ለወደፊት ዕድገታቸው ወሳኝነት እንዳለው ስለሚታመንበት ልዩ ትኩረት የሚያስፈለገው ጉዳይ ነው።

የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ተቋማት ሕፃናት የወደፊት ህይወታቸው መሠረት የሚጥሉበትና ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ የሚደረጉበት ሥፍራዎች ናቸው። እንደዚሁም ሕፃናት በጋራ ተሰባስበው አንድ ላይ በሚውሉበት ወቅት የጋራ ስሜትን በማዳበር ማህበራዊ ጠቀሜታንም የሚያስገኝ ነው። በተጨማሪም እናቶች  በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው በማድረግ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ መስክ በመሳተፍ የሚፈለግባቸውን የአገር ግንባታ ተግባር የበኩላቸውን እንዲወጡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው። ከዚህ አኳያ ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም አስፈላጊውን ግብአት መመደብ በወደፊቱ የአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አስተዋጽኦ ያለው ከመሆኑም በላይ ማህበራዊ እኩልነትን የሚያጠናክር ነው።

የቅድመ - መደበኛ ትምህርት መርሐ ግብር ዕለታዊ እንቅስቃሴ በ3 ዋና ዋና አቅጣጫዎች ይመራል።

እነዚህም፣

1/ ነፃና የታቀደ ጨዋታ፣

2/ ትምህርት እና

3/ ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያለው ሥራ ናቸው።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት + የሚካሄደው ፕሮግራም ተግባራዊ የሚሆነው /ማስተላለፊያ ዘዴው/ (method) በጨዋታ ነው። ይህ የማስተማርያ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በዚህ ዕድሜ ክልል ያሉ ህፃናት ጨዋታን እንደ ዋና ተግባራቸው አርገው ስለሚወስዱትና ሕፃናት በጨዋታ ሲሳተፉ አካላቸው

ይዳብራል፤ አእምሮአቸው ይበለጽጋል፣ ማህበራዊና ስሜታዊ እሴቶቻቸው ይጎለብታል። ስለሆነም ሕፃናት የአካል፣ የመንፈስ፤ የስሜትና የማህበራዊ ኑሮ አስተሳሰብ ብቃታቸው ዳብሮ ለመደበኛው ትምህርት ዝግጁ የሚሆኑት በግልና በጋራ በሚካሄድ ጨዋታ በመሆኑ ለጨዋታው የተለየ ትኩረት ይሰጠዋል።

ሕፃናት ከላይ የተጠቀሱትን ሰብዕናዎች ሊያዳብሩ የሚችሉት በተበታታነ ሁኔታ ሳይሆን በቅድመ - መደበኛ ትም/ተቋማት በመሰባሰብ ነው። በመሆኑ ለዚህ ከፍተኛ ጠቀሜታ ላለው የትምህርት ፕሮግራም በወላጆችና በሕብረተሰቡ ዘንድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

## የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም

ይህ ፕሮግራም ዕድሜያቸው ከ4-5 እና ከ5 — 6 ዓመት የሆናቸው ጤናማና ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት ሁለገብ የሆነና ለዘላቂ ሕይወታቸው መሠረት የሚጥል ዕውቀት፤ ክህሎትና ባህርይ እንዲያገኙ ለማድረግ ሥርዓት ባለው መልኩ ይደራጃል። በዚህ ደረጃ ሕፃናት ከማንኛውም የትምህርት ደረጃ በበለጠ ጥበቃና እንክብካቤ ተደርጎላቸው፤ በአካል፣ በአእምሮ፣ በስሜትና በማኅበራዊ ኑሮ ተገቢውን የዕድገት መሠረት አግኝተው ማደግ እንዲችሉ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ የሚገባው ነው፣ ይህም የወላጆችንና የኅብረተሰቡን የቅርብ ክትትል፤ የመምህራንን ትጋትና ከፍተኛ ጥረት እንዲሁም፤ የመንግሥትን ትኩረት የሚጠይቅ ነው። ለዚህ ፕሮግራም አደረጃጀት፤አመራርና አስተዳደር የሚረዱ ዝርዝር የሥራ መመሪያዎች አሉ። ስለሆነም መመሪያዎቹ በየደረጃው ባሉ ኃላፊዎች፣ ተጠቃሚ ክፍሎችና ሌሎች ባለድርሻዎችን ጨምሮ በሁሉም ዘንድ ታውቀውና እኩል ግንዛቤ አግኝተው ስለአፈጻጸማቸው ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገና አስፈላጊው ሙያዊ ድጋፍ እየተሰጠ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

ስለዚህ ከተቋሙ አመሠራረት ጀምሮ ፕሮግራሙ በምን መልክ መደራጀት እንዳለበት፣ የፕሮግራሙንም ሂደት በብቃት በመምራት የሚፈለገው ውጤት እንዲገኝ የሚያስችሉ መሠረታዊ የመነሻ ዝግጅቶች እንዲኖሩ ማድረጉም አስፈላጊነቱ የጎላ ነው።

## የፕሮግራሙ አወቃቀር

የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ከ4 — 6 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ህፃናት ደረጃውን ጠብቆ ለሁለት ዓመት የሚካሄድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት

ፕሮግራም ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ከ4-5 እንዲሁም 2ኛው ደረጃ ከ5-6 ዕድሜ ላላቸው ሕፃናት አንድ ዓመት የሚካሄድ ፕሮግራም ነው።

ይህ ፕሮግራም ልዩ ፍላጎት ያላቸዉንም ህፃናት የሚያቅፍ ሲሆን፣

ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት የተባሉትም የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

ዕድሜ ላላቸው ለአንድ ዓመት፣

- ማየት የተሳናቸው፣
- መስማት የተሳናቸው፣
- የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ያለባቸው፣
- የስሜት መረበሽ ያለባቸው፣
- የመማር ችግር ያለባቸው፣
- የመናገር ችግር ያለባቸው፣
- የአካል ጉዳት ያለባቸው፣
- ተደራራቢ ጉዳት ያለባቸው፣
- ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው .. ወ.ዘ.ተ ናቸው

## የፕሮግራሙ አደረጃጀት

በቅድመ መደበኛ ትምህርት የሚካሄዱ የፕሮግራም ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

### ጨዋታ

- በሕፃናቱ ምርጫ የሚከናወኑ ጨዋታዎች፤
- በመምህራን መሪነት የሚከናወኑ ጨዋታዎች፤

### በክፍልና ከክፍል ውጭ ተቀናጅተው የሚሰጡ ፕሮግራሞች

- ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋ
- የአካባቢ ሣይንስ ትምህርት
- ሂሣብ

- ሥዕል፣ሙዚቃና የሰውነት ማጐልመሻ
- እንግሊዝኛ
- ህፃናት የሚያከናውኑአቸው ሥራዎች በሁለት ይከፈላሉ። እነዚህም፡-
- ግላዊ ጠቀሜታ የሚሰጡ ሥራዎች
- ማኅበራዊ ጠቀሜታ የሚሰጡ ሥራዎች ሲሆኑ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት በተጨማሪ የሚከተሉት ሥራዎች ይሰጣሉ።

ሀ. ማየት ለተሳናቸው

- የስሜት ሕዋሳትን የማነቃቃትና የማዳበር
- የነፃ እንቅስቃሴ ትውውቅ/ሞብሊቲና ኦረንቴሽን
- የዕለት ተዕለት ክሂልን የማዳበር
- ቅድመ-ብሬል
- ቅድመ-አባከስ
- የእይታ ስሜት ቀስቃሽ ክንውን /በመስማት እንዲያዳብሩ/

ለ. መስማት ለተሳናቸው

- ከናፍረ-ንባብ
- የማዳመጥ ልምድ
- ንግግር
- ቋንቋ
- የምልክት ቋንቋና የጣት ፊደል ቆጠራ
- ረዳትን የመስሚያ መሣሪያዎች የአጠቃቀም ልምምድ

ሐ. የአእምሮ ዕድገት ዝግመት

- እንቅስቃሴ
- እጅን እንደተፈለገ የመጠቀም ልምምድ
- ጨዋታ

- ቋንቋ
- ማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት
- ራስን የመርዳት ክሂሎች
- ሥነጥበብና ሙዚቃ

**የፕሮግራም፡ ወቅት/ካሌንደር/**

- የአንድ ዓመት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ከ203 — 206 ቀናት ይኖሩታል።
- የአንድ ዓመት የቅድመ መደበኛ ፕሮግራም 30 ሳምንታት ሆኖ በሣምንት 5 ቀናት /ከሰኞ-ዓርብ/ ይካሄዳል። በሣምንት 25 ክፍለ ጊዜያት ሲኖሩት፣ የአንድ ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 30 ደቂቃ ሆኖ በመካከል የ5 ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል፣
- የተቀመጠው የክፍለ-ጊዜ ብዛት እንደ ሕፃናቱ ፍላጎትና ከአካባቢውና ከትምህርቱ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ሊሻሻል ይችላል።

ሀ. ለደረጃ አንድ ከ/4-5 ዓመት ዕድሜ ላላቸው/ የአንድ ክፍለ - ጊዜ ርዝመት 25 ደቂቃ ሆኖ በክፍለ ጊዜያት መካከል የ5 ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል።

ለ. ለደረጃ ሁለት ከ/5-6 ዓመት ዕድሜ ላላቸው/ የአንድ ክፍለ - ጊዜ ርዝመት 30 ደቂቃ ሆኖ በክፍለ ጊዜያት መካከል የ5 ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል።

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም በሙሉ ቀን ይካሄዳል።
- በመጀመሪያ ሴሚስተር መጨረሻ ላይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት ለ15 ቀናት ዕረፍት ዝግ ይሆናሉ።

## የክፍለ ጊዜያት ሥርጭት፤

### ሣምንታዊ የክፍለ ጊዜ ሥርጭት፤/ የክፍለ- ጊዜ ስርጭት

| ተ/ቁ | የፕሮግራም ዓይነት | ለደረጃ አንድ | ለደረጃ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|
| | | ከ4-5 ዓመት* | ከ5-6 ዓመት* | ምርመራ |
| 1 | ጨዋታ | 10 | 8 | |
| 2 | ትምህርት | | | |
| | – ቋንቋ | 3 | 4 | |
| | – የአካባቢ ትምህርት | 2 | 2 | |
| | – ሂሣብ | 2 | 2 | |
| | – ሙዚቃ | 2 | 2 | |
| | – የሰውነት ማጐልመሻ | 2 | 2 | |
| | – የሥነ ሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ | 2 | 3 | |
| 3 | – ሥራ / ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያለው/ | 2 | 2 | |
| | ድ ም ር | 25 | 25 | |

*ከ4-5 ዓመት ማለት ዕድሜያቸው 4 ዓመት ያለፋቸውና እስከ 5 ዓመት የደረሰ ማለት ነው።

*ከ5-6 ዓመት ማለት 5 ዓመት ያለፋቸውና እስከ 6 ዓመት የደረሱ ሕፃናት ማለት ነው።

## ማሳሰቢያ፣

1 መደበኛውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም መከታተል የሚችሉ ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት በተለየ ክፍል ውስጥ ሆነው ልዩ ክህሎቶችን ከተከታተሉ በኋላ ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው በፕሮግራሙ ላይ ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ። ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው ፕሮግራሙን እኩል መከታተል የማይችሉት ግን በተለየ ክፍል ውስጥ በመሆን አግባብ ያለውን ፕሮግራም ይከታተላሉ። ለዝርዝር ማብራሪያ የልዩ ትምህርት መመሪያ ይመለከቷል።

2 ለየቡድኑ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በዕለታዊ የፕሮግራም መርሃ ግብር ላይ እንደተመለከተው የጨዋታ፣ የትምህርትና የሥራ ጊዜ ርዝመት እንደ አስፈላጊነቱ የተለያየ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

## ዕለታዊ ፕሮግራም መርሃ ግብር

| ተቁ | የፕሮግራሙ ዓይነት | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 |
|---|---|---|---|
| | | ከ4-5 ዓመት | ከ5-6 ዓመት |
| 1 | የመቀበያ ሰዓት | 2፡00 - 3፡00 ሰዓት | 2፡00 - 3፡00 ሰዓት |
| 2 | ለትምህርት ቅድመ ዝግጅት | 3፡00 - 3፡05 “ | 3፡00 - 3፡05 “ |
| 3 | ትምህርት | 3፡05 - 3፡30 “ | 3፡05 - 3፡35 “ |
| 4 | ለትምህርት ቅድመ ዝግጅት | 3፡30 - 3፡35 “ | 3፡35 - 3፡40 “ |
| 5 | ትምህርት | 3፡35 - 4፡00 “ | 3፡40 - 4፡10 “ |
| 6 | ለቁርስ ዝግጅትና ቁርስ መመገቢያ | 4፡00 - 4፡40 “ | 4፡10 - 4፡50 “ |
| 7 | ዕረፍት/ነፃ ጨዋታ/ | 4፡40 - 5፡40 “ | 4፡50 - 5፡50 “ |
| 8 | የክፍል ውስጥ ጨዋታ | 5፡40 - 6፡05 “ | 5፡50 - 6፡20 “ |
| 9 | የክፍል ዝግጅት | 6፡05 - 6፡15 “ | 6፡20 - 6፡30 “ |
| 10 | የምሣ ዝግጅትና መመገቢያ | 6፡15 - 7፡15 “ | 7፡30 - 8፡30 “ |
| 11 | ከመኝታ መነሳትና መፀዳዳት | 8፡15 - 8፡30 “ | 8፡30 - 8፡45 “ |
| 12 | የትምህርት ቅድመ ዝግጅት | 8፡30 - 8፡35 “ | 8፡45 - 8፡50 “ |
| 13 | ትምህርት | 8፡35 - 9፡00 “ | 8፡50 - 9፡20 “ |
| 14 | የውጭ ጨዋታ | 9፡00 - 9፡50 “ | 9፡20 - 9፡50 “ |
| 15 | ወደ ቤት ሽኝት | 9.50 -10.25 “ | 9፡50 -10፡25 “ |

16. ሥራ /ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያለው ተግባር/ 2 ክ/ጊዜ ሆኖ በመምህራኑ በሚዘጋጀው ፕሮግራም መሠረት 50 ደቂቃ የሚሸፈን ይሆናል፣

* ማሳሰቢያ 1 / በሣምንት ሁለት ቀናት ለትምህርት ከተያዘው ጊዜ ውስጥ የቡድን ሥራ የሚሠሩበት ሰዓት ይሆናል።

2/ የመርሐ ግብሩ የመጀመሪያና የመጨረሻ ሰዓት እንደ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

**የመምህራን የሥራ ሰዓት መጠን**

- ሕፃናትን በአግባቡ ለማሳደግ፤ ለመንከባከብና ለመደበኛ ትምህርት በብቃት ለማዘጋጀት ለአንድ መምህር/ት/ በሳምንት የሚኖሩት/ራት የሥራ ሰዓት መጠን የሕፃናቱ ምሳና መኝታ በየቤታቸው ከሆነ በሳምንት 30 ሰዓት ይሆናል።
- ይህም
    - 5 ሰዓት ጠዋት ሕፃናትን ለመቀበል፣
    - 13 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ለጨዋታ፤ ለትምህርትና ሥራ ነክ ለሆኑ ፕሮግራሞች፣
    - 11 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ለቁርስ፤ለእረፍት፤ ለክፍል ዝግጅትና ለመሸኛ የሚውለውን ጊዜ ያጠቃልላል።
    - ለሕፃናት ምግብና መኝታ በአፀደ ሕፃናቱ ውስጥ የሚሰጥ ከሆነ በሳምንት 40 ሰዓት ይሆናል።

ይህም በዝርዝር ሲታይ፣

- 5 ሰዓት ጠዋት ሕፃናትን ለመቀበል፣
- 13 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ለጨዋታ፤ ለትምህርትና ሥራ ነክ ለሆኑ ፕሮግራሞች፣
- 21 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ለቁርስ፣ለምሳ፣ለመፀዳዳት፣ ለመኝታ፣ ለእረፍት፣ ለክፍል ዝግጅትና ለመሸኛ የሚውለውን ጊዜ ያጠቃልላል።

## የማስተማር ዘዴዎች

በቅድመ መደበኛ ፕሮግራም ለሕፃናት በጨዋታ መልክ የሚሰጡአቸው ተግባራት ከሕፃናቱ የአእምሮና የአካል ብቃት ወዘተ ጋር የሚጣጣሙና ለወደፊት ዕድገታቸው የጐላ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው። ስለሆነም በዚህ ደረጃ ለሕፃናት የሚሰጠው መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ሳይሆን ለሕፃናቱ ዕድገት መሠረት የሚሆኑ ክንውኖች (developmental activities) ስለሆኑ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች በሙሉ የሕፃናትንና የመምህራን የጋራ ተሳትፎ የሚጠይቁ ናቸው። ስለሆነም በግልም ሆነ በጋራ እንዲካሄዱ የሚዘጋጁ እንቅስቃሴዎች የሕፃናትን የአካል የአእምሮ የስሜትና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ መሆን አለባቸው።

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ህፃናት የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት ለእነርሱ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ የማስተማር ዘዴዎች ተደግፈው ሲቀርቡ ነው።

በዚህ ደረጃ መምህራን የሚከተሉትን የማስተማር ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

- የቡድን ጫወታ
- የግል ጫወታ
- ሚና ጫወታ
- ሠርቶ ማሳየት
- የመስክ ጉብኝት /በመምህራን የቅርብ ክትትል/ ማወያየት፣
- የቃል ዘገባ
- ገለጻ /ሕፃናትን አሳታፊ የሆነ/ወዘተ ናቸው።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ሕፃናት የሚገመገሙት ፈተና በመስጠት ሳይሆን በተከታታይ የምዘና ዘዴ ነው።

## ከመምህራን የሚጠበቅ ባህሪ

- ርህራሄ
- ትዕግስት
- ለህፃናት ልዩ ፍቅር ያላቸው
- ደባል ፀባይ የሌላቸው
- ጥሩ ስነምግባር

- ለሙያው ያለው ፍቅር
- የአካባቢውን ባህልና ወግ የሚያውቅ

የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን የአፍ መፍቻና የእንግሊዝኛ ቋንቋዎችን ጨምሮ ስለሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት፣ ስለሚያስተምሩዋቸው ሕፃናትና በመካከላቸው ሊኖሩ ስለሚችሉ የችሎታና የፍላጐት ልዩነቶች እና እንደዚሁም ለልዩነቶቹ አያያዝ አስፈላጊ የሆኑ ሙያዊ እውቀትና ክህሎት መጨበጥ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም በሙያዊ ተግባር ክንውን ሂደት ይህን እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ከተገቢው ሙያዊ ሥነ ምግባር ጋር በማቀናጀት በሕፃናት እንቅስቃሴ ፕሮግራም ላይ በተሟላ መልክ መሳተፍ ይገባቸዋል።

- ለቅድመ መደበኛ ፕሮግራሙ የሚሆኑ ክንውኖችን ከሕፃናት የአካል የስሜትና ማህበራዊ ወዘተ ዕድገት ጋር በማገናዘብ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉትን በማቀድ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው።

**የቅድመ መደበኛ መርሐ-ግብርን ያጠናቀቁ ሕፃናት ባህርይ፣**

- በአካልና በአእምሮ የበለፀጉ፣ ስሜትን መግለጽና ውበት ማድነቅ የሚችሉ፣
- ለምርምር፣ለፈጠራና ለሥራ ፍቅር ያላቸው፣ በራስ የሚተማመኑና በሥነ ሥርዓት የታነፁ፣
- ሆሂያትንና አሃዞችን በሥርዓት መለየትና መቅረጽ፣ ተራን ጠብቆ ሃሣብን መግለጽና ማዳመጥ የሚችሉ፣
- በአካባቢያቸው ለማህበራዊ ኑሮ የነቁና ለመደበኛ ትምህርት የተዘጋጁ ናቸው።

**የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት የሚቋቋሙባቸው አካባቢዎችና የሕንፃው ሁኔታ**

**የቦታ አመራረጥ፤**

- አካባቢው የፀዳና ለሕፃናት ተስማሚ የሆነ ንጹህ አየር ያለው፣ ከቆሻሻ መጣያ፣ ከፍሳሽ፣ ከወንዞች፣ ከኩሬዎች፣ ከረግረግና ከገደል የራቀና ሕፃናትን የሚተናኮሉ አውሬዎችና ነፍሳት የሌሉበት፤
- ለትራፊክ አደጋ የማያጋልጥ፤
- በቀላሉ ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚገኝበት፤

- ከመንገድ ዳር ገባ ያለ፤
- ከመጠጥ ቤቶች የራቀ፤
- ቢቻል በአቅራቢያው ሆስፒታል፤ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ያለው ሆኖ ተላላፊ በሽታ ከሚከላከሉ እንደ ሳንባ ነቀርሳ መከላኪያና ከመሳሰሉት የጤና ድርጅቶች አቅራቢያ ባይሆን የተሻለ ነው።
- ፀጥታ የሰፈነበት አካባቢ፤ የእንጨት መሰንጠቂያ፤ ወፍጮ ቤት፣ ሙዚቃ ቤት … ወዘተ ከመሳሰሉት የራቀ፤
- ሰፊ ቦታና በቂ የመጫወቻ ሥፍራ ያለው፤
- ለሕፃናቱ እንዳይርቅ ከቤታቸው በአማካይ ከአንድ ኪሎ ሜትር ያልራቀ ቦታ ሊመረጥለት ይገባል።
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ሕንፃዎች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት ከስሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላና ወዘተ ማቴሪያሎች ሊሠሩ ይችላሉ።

## የምድረ ግቢ ገጽታና አደረጃጀት

- አጥሩ በአካባቢው ከሚገኙ ጥሬ ዕቃዎች የተሠራ ሆኖ ቁመቱ ከ1.5 ሜትር ያላነሰና በሕፃናት ላይ አደጋን የማያስከትል መሆን አለበት።
- አጥሩ አሾሃማ አጥር መሆን የለበትም፤
- ለጥላና ለመዝናኛ የሚያገለግሉ ዛፎች ሊኖሩት ይገባል፤
- ግቢው ልዩ ልዩ የመጫወቻና የአካል ማጐልመሻ መሣሪያዎች ያሉት ሆኖ የመሬቱ ወለል ለሕፃናቱ ልዩ ልዩ የአካል እንቅስቃሴ የሚያመች የተስተካከለ መሆን አለበት።
- ድብብቆሽ የሚጫወቱበት፣ የአሸዋ ሣጥን፣ የአበባና የአትክልት ቦታዎች ያሉት፣ሆኖ ስለዕፅዋት፣ ስለዘር፣ ስለተከል ወዘተ. ሊማሩበት የሚያስችል መሆን አለበት።

### የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት መጠን

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት  በአንድ ክፍል ውስጥ ከ10-40 ሕፃናት ማስተናገድ አለበት። አንድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም እያንዳንዳቸው ከ36-53 ካ.ሜ የሆኑ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል። በእነዚህም ክፍሎች ውስጥ በአንድ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት አንድ መምህር /ት/እና አንድ ረዳት መምህር/ት/ ያስፈልጋሉ።

### የምድረ ግቢና የሕንፃዎች አደረጃጀት

– የምድረ ግቢና የሕንፃ አደረጃጀት ለልዩ ፍላጐት ተማሪዎች በሚመች መልኩ ይደራጃል ይህም።

- የምድረ ግቢው ስፋት እንደ መማሪያው ክፍሉ ብዛት ከ500-3000 ሜትር ካሬ ያለው ይሆናል።
- በግቢው ውስጥ የሕንፃው ወይም የህንፃዎቹ አቀማመጥ ለሕፃናቱ የውጭ መጫወቻዎች ዝግጅት እንዳያውክ ሆኖ ይሠራል።
- የሕፃናት ክፍሎች ሲሠሩ ለያንዳንዱ ሕፃን ከ1.55 ሜትር ካሬ ያላነሰ ቦታ እንዲኖር ሆኖ ይሠራል።
- የቤቱ በርና መስኮቶች አቀማመጥ ለከፍተኛ ቅዝቃዜ የማያጋልጡ ይሆናሉ።
- ደረጃዎች እንዳይኖሩት ወይም እንዳይበዙበት ተደርጐ ይሠራል፤
- ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት ታሳቢ ያደረገ ህንፃ መሆን አለበት።
- መስኮቶቹ ሕፃናት ወደ ውጭ በሚገባ ማየት የሚያስችሏቸው በሩም ክብደት የሌለውና ሳይፈለግ እንዳይዘጋ ከግድግዳው ጋር የሚያያዝ ማጠበቂያ ሊኖረው ይገባል።

– የቤቱ የውስጥም ሆነ የውጭ ግድግዳ ከወለሉ ቢያንስ፣ 1 ሜትር ከፍታ ድረስ ሻካራ ያልሆነና በሕፃናቱ /አካላት ላይ / እጅ ጉዳት የማያደርስ መሆን አለበት።

– የመፀዳጃ ቤቱ ጣራና ግድግዳ ያለው፤ በቂ አየርና ብርሃን የሚያስገባ፤ ወለሉ በቀላሉ ለማጽዳት የሚቻል፤ የጉድጓዱ ቀዳዳ በሕፃናቱ መጠን ግምት ውስጥ

አስገብቶ የተሠራና መግጠሚያ ያለው፣ የእጅ መታጠቢያም አጠገቡ ያለው መሆን አለበት።

- ክፍሎቹ እንደ አካባቢው ሁኔታ ብርሃንን፤ ሙቀትን፤ ብርድን፤ ዝናብንና ትንኞችን ለመቆጣጠር በሚያስችሉ እንደ መጋረጃ፣ መስተዋትና እንዲሁም በሽቦና ከመሳሰሉት የተሠራ የወንፊት መስኮት ሊኖራቸው ይገባል።

## የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ሊኖሩት የሚገባ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች

| ተ/ቁ | የሕንፃው ክፍሎች | ባለ 1 ክፍል | ባለ 2 ክፍል | ባለ 3 ክፍል | ባለ 4 ክፍል | ባለ 5 ክፍል | ባለ 6 ክፍል | የአንድ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር | የመማሪያ ቦታ በህንፃ በካሬ ሜትር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ ክፍል | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 36-56 | 1.55 ሜካ |
| 2 | ጽ/ቤት ቢሮ | | | | | | | 4 X4=16 | |
| 3 | ዕቃ ግ/ቤት | | | | | | | 2.8X2.5=7 | |
| 4 | የምግብ ማብሰያ | | | | | | | 5X5.6 | |
| 5 | ዕቃ ክፍል | | | | | | | 2.6X2. | |
| 6 | የሕፃናት መፀዳጃና መታጠቢያ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 9X5 | |
| 7 | የመምህራንና የሠራተኞች መፀዳጃ | | | | | | | 2X2.4 | |
| 8 | የሕፃናት ማረፊያ ክፍል | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 6X5 | |
| 9 | ሁለገብ አዳራሽ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 8X7 | |
| 10 | የጥበቃ ቤት | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2.45X2.45 | |
| 11 | የመምህራን ማረፊያ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 4X5 | |
| 12 | የገ/ያዥ ቢሮ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2.8 X2.5 | |
| 13 | የመመገቢያ | | | | | | | 5×8=40 | |

| ተ/ቁ | የሕንፃው ክፍሎች | ባለ 1 ክፍል | ባለ 2 ክፍል | ባለ 3 ክፍል | ባለ 4 ክፍል | ባለ 5 ክፍል | ባለ 6 ክፍል | የአንድ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር | የመማሪያ ቦታ በህንፃ በካሬ ሜትር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ክፍል | | | | | | | | |
| 14 | የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫና የጽዳት ዕቃ ማስቀመጫ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3.50X5.70 | |
| 15 | የምግብ ዕቃ ክፍል | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3.40X3.70 | |
| 16 | ልዩ ልዩ ኮርነሮች /ማዕዘን/ ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት የንግግር ወጌሻ መስጫ ክፍል | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 4X3.5 | |

**ለልዩ ልዩ ክፍሎች አስፈላጊ መሣሪያዎች**

**ለአንድ መማሪያ ክፍል የሚያስፈልጉ ቋሚ መሣሪያዎች፣**

| ተቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | መጠን በሳ/ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጠመኔና ጥቁር ሠሌዳ | 1 | 50 X 100 | |
| 2 | የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ | 1 | 50 X 100 | |
| 3 | የመምህሩ ወንበር | 1 | 40 X 56 X 78 | |
| 4 | የመምህሩ ጠረጴዛ | 1 | 80 X 100 X 74 | |
| 5 | የሕፃናት ወንበሮች | 40 | 34 X 24 X 27 | |
| 6 | የሕፃናት ጠረጴዛዎች | 10 | 68 X 98 X 75 | |
| 7 | ዕቃ መደርደሪያዎች | 3 | 10 X 200 X 40 | |
| 8 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ | 1 | | ከሳጠራ/ከፕላስቲክ የተሠራ |

ከዚህ ሌላ ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት የሚከተሉት መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ። በዚህም መሠረት፤-

**መስማት ለተሳናቸው ሕፃናት**

- መሣሪያዎች መንቀሳቀሳቸውን የሚያመለክት ብርሃን ማሳያት፤
- የማስጠንቀቂያ ደወል ለመተካት እንደባትሪ ያሉ ነገሮች እንዲታይ ማድረጊያ፤
- በከፊል ለሚሰሙት ድምፅ አጉሊ መሣሪያ መጠቀም ለምሳሌ፡-ረዳት የመስሚያ መሣሪያ
- ድምፅ - አልባ የታይፕ መኪና መጠቀም
  ሌሎች መሣሪያዎች
- የዕይታ መሣሪያዎች ብርሃን አስተላላፊ ወረቀት፤ ፊልም፤ ካብሽን፤ ስላይድ፤ፊልም፣ ቻርት መሳሪያ

**ማየት ለተሳናቸው ህፃናት**

- አባከሰ
- ብሬል
- ስሌት
- ስታይለስ
- ዘንግ
- ቴፕሪከርደር

**የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ላለባቸው ህፃናት**

- ቴሌቪዥን
- DVD
- የፊዚዩቴራፕ ኳሶች

**ለተግባራዊ ትምህርት የሚያገለግሉ መሣሪያዎች**

ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የተዘጋጁት መሣሪያዎች ልዩ ፍላጐት ላላቸው ሕፃናትም ጭምር ያገለግላሉ።

**የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ዕቃዎች**

| ተራ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | የጥጥ ዕቃ | እንደተገኘ |
| 2 | ሶስት መዓዘን ፋሻዎች | |

| ተራ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 3 | ጥቅል ፋሻዎች | |
| 4 | የተቀቀሉ የጨርቅ ፓዶች | |
| 5 | የተቆራረጡ በራዚዎች | |
| 6 | ከፋሻ ጋር የተያያዙ ፓዶች | |
| 7 | የላስቲክ ፋሻ | |
| 8 | የእጅ ፎጣ | |
| 9 | መጠነኛ የእንጨት /ስፕሊንት/ | |
| 10 | የሕፃናት መመርመሪያ አልጋ | 1 |
| 11 | ፍራሽ | 1 |
| 12 | ብርድ ልብስ | 2 |
| 13 | አንሶላ | 4 |
| 14 | የመድኃኒት ስኒ | 2 |
| 15 | መቀስ | 2 |
| 16 | ወረንጦ | 2 |
| 17 | መርፌ ቁልፎች | እንደተገኘ |
| 18 | የቁስል መለጠፊያ ፕላስተር | " |
| 19 | የማስታወሻ ደብተር | " |
| 20 | ሳሙና ከነመቀመጫው | " |
| 21 | የመጠጫ ኩባያ | 2 |
| 22 | ማህን ትንሽ /ኪድኒ ድሽ/ | 2 |
| 23 | ተርንኪ/ለስቲክ/ | 2 |
| 24 | የሕክምና ኩራዝ | 2 |

**ማሳሰቢያ፣**

ከላይ ከተዘረዘሩት መካከል በቁጥር ላልተገለጹ ህክምና ዕርዳታ መስጫ/ዕቃዎችን ብዛት እንደ ሕፃናቱ ብዛት ግምት ውስጥ ያስገባ መጠን መሆን አለበት።

**ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል የሚያሰፈልጉ መድኃኒቶች**

| ተ. ቁ | የመድኃኒቱ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | የጥጥ ዕቃ | ቢያንስ በፓድ የታሸገ |
| 2 | ሶስት ማዕዘን ፋሻዎች | " |
| 3 | ጥቅል ፋሻዎች | " |
| 4 | የተቀቀሉ የጨርቅ ፓዶች | " |
| 5 | የተቆራረጡ ንፁህ ጨርቆች | " |
| 6 | የላስቲክ ፋሻ | " |
| 7 | የእጅ ፎጣ | " |
| 8 | የሕጻናት ማረፊያ አልጋ | 1 |
| 9 | ስፖንጅ ፍራሽ | 1 |

| | | |
|---|---|---|
| 10 | ብርድ ልብስ | 1 |
| 11 | ጥንድ አንሶላ | 1 |
| 12 | አልኮል፣አዩዲንና ጀንሺያን ባዩዋሌት | እያንዳንዳቸው በጠርሙስ |
| 13 | መቀስ፣ወረንጦ | ቢያንስ ሁለት፣ሁለት |
| 14 | መርፌ ቁልፍ | አንድ ፓኬት |
| 15 | የቁስል ማጠቢያ (አንቲሴፕቲክ) | “ |
| 16 | ባለመድኃኒት የቁስል መለጠፊያ ፕላስተር | “ |

**ማሳሰቢያ፣**

ከላይ የተዘረዘሩ ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች ብዛት በተቋሙ በሚማሩ ሕፃናት ቁጥር ተመጣጣኝ መሆን አለበት።

### ለማዕድ ቤት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች

| ተ ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ማንቆርቆሪያ | 1 |
| 2 | ብረት ድስት | 1 |
| 3 | የሸክላ ድስት | 2 |
| 4 | ቡሃቃ ( ማቡኪያ ) | 4 |
| 5 | ባልዲዎች | 4 |
| 6 | የዕቃ መደርደሪያ | 1 |
| 7 | ማብሰያ ምድጃ | 1 |
| 8 | ትናንሽ ማንኪያዎች | 40 |
| 9 | ትናንሽ ማብሰያ ሣህኖች | 40 |
| 10 | የሻይ፣የውሃና የወተት ኩባያ | 40 |
| 11 | የዳቦ ማቅረቢያ ትሪ | 5 |
| 12 | ጭልፋዎች | 3 |
| 13 | ማቡኪያ ሣህን ወይም ገበቴ | 1 |
| 14 | ወንፊትና ሰፌድ | 2 |
| 15 | ቢላዎች | 5 |
| 16 | መጥበሻዎች | 2 |
| 17 | የዕቃ መወልወያ ንጹህ ጨርቆች ባለ 1 ሜትር | 5 |

### አላቂ የመጫወቻ ዕቃዎች

| ተ ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | የተሠራበት ማቴሪያል |
|---|---|---|---|
| 1 | የመገንቢያ ብሎኮች | 4 ሴት | ከሸክላ፣ፕላስቲክ፣እንጨት |
| 2 | አሻንጉሊቶች | እንደተገኘ | ከጨርቅ፣ፕላስቲክ |

| ተቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | የተሠራበት ማቴሪያል |
|---|---|---|---|
| 3 | ለቤተሰብ ኮርነር የሚያስፈልጉ ሲኒዎች | “ | ከሸክላ፣ከቆርቆሮ |
| | ጀበናዎች | “ | ከሸክላ፣ከቆርቆሮ |
| | ማንኪያዎች | “ | ከሸክላ፣ከቆርቆሮ |
| | ሣህኖች | “ | ከሸክላ፣ከፕላስቲክ፣ከቆርቆሮ |
| | ትናንሽ የአሻንጉሊት አልጋዎች | “ | ከእንጨት፣ከፕላስቲክ |
| 4 | ለሕክምና ኮርነር የሚያስፈለጉ | | |
| | ▪ ሽርጦች | 4 | ከጨርቅ |
| | ▪ ስሪንጆች | እንደተገኘ | ከጎማ፣ፕላስቲክ |
| | ▪ ማዳመጫዎች | “ | ከዕንጨት |
| | ▪ ፋሻዎች | 4 | ከጨርቅ |
| | ▪ የመድኃኒት ብልቃጦች | እንደተገኘ | ከፕላስቲክ፣ከጠርሙስ |
| | ▪ እንደ ስትሬቸር የሚያገለግሉ አልጋዎች | “ | ከሣጠራ፣ከእንጨት |
| 5 | ለሱቅ ኮርነር የሚያስፈልጉ ሚዛኖች | “ | ከፕላስቲክና ከብረት |
| | ▪ ሚዛን | “ | ከፕላስቲክ፣ከብረት |
| | ▪ ባዶ የእስክሪቢቶ ቀፎዎች | እንደተገኘ | ከፕላስቲክ |
| | ▪ ባዶ የክብሪት ቤቶች | “ | ከእንጨት |
| | ▪ የተለያዩ የሕፃናት ልብሶች | “ | ከጨርቅ |
| | ▪ ቆርኪዎች | “ | ከቆርቆሮ |
| | ▪ ልዩ ልዩ የቤት ቁሳቁሶች | “ | ከአፈር፣ከሲሚንቶ |
| | ▪ የገንዘብ ኖቶችና ሳንቲሞች | “ | ከወረቀት፣ከፕላስቲክ |
| 6 | ለሳይንስ ኮርነር<br>▪ ልዩ ልዩ የሳይንስ ኪቶች | “ | ከወረቀት፣ ከፕላስቲክ<br>ከወረቀት፣ከዕንጨት፣ከቆርቆሮ፣ከጭቃ፣ወዘተ |
| 7 | ለኅብረተሰብ ኮርነር<br>▪ ልዩ ልዩ ሥዕሎችና የአካባቢ አልባሳት | “ | ከጨርቅ፣ ወረቀት፣ጭቃ |
| 8 | ለቋንቋና የንባብ ኮርነር<br>▪ ሥዕሎች፣ጋዜጦችና የሕፃናት መፃሕፍት | እንደተገኘ | |
| 9 | ለሂሣብ ኮርነር<br>▪ ልዩ ልዩ ቁጥሮች መቁጠሪያ መማሪያዎችና ምልክቶች | | ከፕላስቲክና ከእንጨት፣ከወረቀት ከጭቃ |
| 10 | ለሙዚቃ ኮርነር<br>▪ ልዩ ልዩ የአካባቢና ባህላዊ መሣሪያዎች | “ | ከዕንጨት፣ከቆዳ፣ከጅማት ክር |
| 11 | ለሥነ ሥዕል ኮርነር | | ከጨርቅ፣ከእንጨትና ከሸክላ |

## ቋሚ የውጭ መጫወቻ መሣሪያዎች

| ተ/ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | መጠን | ዓይነት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኳሶች | 10 /ለአርባ ሕፃናት/ | | | 1 ኳስ ለአራት ሕፃናት |
| 2 | ጉማዎች | 10 | | | |
| 3 | ኸርዋኸርዌ | 2 | | | |
| 4 | ሚዛን | 2 | | | |
| 5 | ሸርተቴ | 2 | | | |
| 6 | ሜራጎራውንድ | 2 | | | |
| 7 | መሰላል | 2 | | | |
| 8 | የመሹለኪያ ቱቦዎች | 2 | | | |
| 9 | የአሸዋ ሣጥን | 2 | | | |

**ማሳሰቢያ፣**

ከላይ የተገለፀው እያንዳንዱ የዕቃ ዓይነት ብዛት ለ40 ሕፃናት ሲሆን የሕፃናቱ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የዕቃዎቹም ብዛት እንደሚጨምር ይጠበቃል።

## ለርዕሰ መምህር ቢሮ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች

| ተ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | መጠን | ዓይነት |
| 1 | ወንበር | 4 | 40x56x68 | |
| 2 | ባለኪስ ጠረጴዛ | 1 | 80x50x74 | |
| 3 | የመፅሐፍ መደርደሪያ | 1 | 10x200x40 | |
| 4 | የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ | 1 | | ከሳጠራ/ከፕላስቲክ የተሠራ |
| 5 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ | 1 | | |
| 6 | የእርሳስ መቅረጫ | 1 | | |
| 7 | ስቴፕለር | 1 | | |
| 8 | ማስመሪያ | 1 | | |
| 9 | መዛግብት | እንደአስፈላጊነት | | |
| 10 | የፋይል አቃፊዎች | “ | | |
| 11 | ወረቀት | “ | | |
| 12 | ክላስር | “ | | |
| 13 | የወረቀት መርፌ | “ | | |
| | ካርቦን | | | |

## የሰው ኃይል ምደባ

**የመምህራንና ሠራተኞች ምደባ፤**

- የቅድመ መደበኛ ተቋም ርዕሳነ መምህራን፤ መምህራንና ሞግዚቶች ሴቶች ቢሆኑ ይመረጣል፣
- አንድ መምህር / ት 40 ሕፃናትን ያስተናግዳል/ታስተናግዳለች፣
- 40 ሕፃናት ለምታስተምር መምህርት አንድ ረዳት መምህርት ትመደባለች፣

  አንድ ሞግዚት ለ40 ሕፃናት ትመደባለች፣
- ለአንድ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም እንደ ክፍሎችና ሕፃናቱ ብዛት የሰው ኀይል ይመደባል።

**የመምህራንና ሠራተኞች ብዛት፣**

| የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም መጠን | የሕፃናት | የር/መምህር | የመምህራን | የረዳት መምህራን | የሞግዚት | የጥበቃ ሠራተኞች | ተላላኪ | የጽዳት ሠራተኞች | የጤና ባለሙያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የመማሪያ ክፍል | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት | | ብዛት | ብዛት | |
| ባለ 1 መማሪያ ክፍል | 40 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 |
| ባለ 2 መማሪያ ክፍል | 80 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 |
| ባለ 3 መማሪያ ክፍል | 120 | 1 | 3 | 3 | 3 | 2 | 1 | 2 | 1 |
| ባለ 4 መማሪያ ክፍል | 160 | 1 | 4 | 4 | 4 | 2 | 1 | 2 | 1 |
| ባለ 5 መማሪያ ክፍል | 200 | 1 | 5 | 5 | 5 | 2 | 1 | 2 | 1 |
| ባለ 6 መማሪያ ክፍል | 240 | 1 | 6 | 6 | 6 | 2 | 1 | 2 | 1 |

**ማሳሰቢያ፣**

የህፃናቱ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የሰው ኃይል ምደባው በተገለጸው ሥሌት መሠረት የሚጨምር ይሆናል።

* ከአንድ እስከ ሁለት መማሪያ ክፍሎች ላላቸው ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት በሥራ ልምድና በአገልግሎት ዘመን ብልጫና በሥራ ትጋት የተሻለ/ች አንድ/ዷት

መምህር/ት ከማስተማር ሥራው/ዋ በተጨማሪ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ኃላፊ መምህር በመሆን ያገለግላል/ ታገለግላለች። ነገር ግን ከሁለት የመማሪያ ክፍል በላይ ላላቸው ትምህርት ተቋማት ራሱን የቻለ ኃላፊ ይመደብለታል።

" በአንድ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ከሚገኙት ሕፃናት ውስጥ ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት ብዛት ከ5%-10% ቢሆን ይመረጣል።

**የመምህራንና የሠራተኞች የትምህርት ደረጃ፣**

- የመምህራን የትምህርት ደረጃ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ዘርፍ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች፣
- የረዳት መምህር/ት/የት/ደረጃ 10ኛ ክፍል አጠናቆ/ቃ በአፀደ ሕፃናት ትምህርት በሰርተፊኬት የተመረቀ/ች፣
- ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸውን ሕፃናት ለማስተማር ከላይ ከተገለጸው መመዘኛ በተጨማሪ በልዩ ትምህርት አጫጭር ሥልጠናዎች የወሰዱ መምህራን ሊሆኑ ይገባል።
- የንግግር ወጌሻ የ10ኛ ክፍልን አጠናቅቆ/ቃ/በአፀደ ሕፃናት መምህርነት የሰለጠነ/ች/ የምስክር ወረቀት ያለው /ያላት/እንዲሁም በልዩ ትምህርት የሰለጠነ/ች/፣
- የሞግዚት የት/ደረጃ 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቀች ሆኖ ቢቻል በሥርዓተ ምግብ ሥልጠናና በምግብ ዝግጅት ልምድ ያላት፣
- የጥበቃ ሠራተኞች የት/ደረጃ ቢያንስ 8ኛ ክፍል ያጠናቀቁ ይሆናሉ፣
- ማሳሰቢያ፣ በልዩ ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን የሚያስፈልጉት ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት ባሉበት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ነው።

**ልዩ ልዩ አስፈላጊ የቅድመ መደበኛ የትምህርት መመሪያዎች**

- የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣
- መርሀ ትምህርት፣
- የመምህሩ መምሪያ፣
- የተማሪው የንባብ፤ የተረትና ሥዕላዊ መጻሕፍት፣
- ልዩ ልዩ የት/መርጃ መሣሪያዎች፣

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት መመሪያ፣
- ማየት የተሳናቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
- መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
- የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ያለባቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣

## ሕግ ነክ ሰነዶች

- ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፣
- የትምህርት ሕግ፣
- የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣
- ስለግል የት/ተቋሞች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ፣
- የማዕከልና/የክልል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጠን ለመወስን የወጣ አዋጅ 4/71/98
- የተሻሻለው አዲሱ የሠራተኞች ህግ አዋጅ ቁጥር 377/1996

## የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ከወላጆች፣ ከህብረተሰቡና ከአመራር ጋር ሊኖረው የሚገባ ግንኙነት

### 1.16.1 የወላጆች ሚና

የወላጆች ተሳትፎ በትምህርት ቤት ውስጥ ለልጆች ስኬታማነት አስተዋጽዖ ከሚያበረክቱት በጣም ጉልህ ነገሮች መካከል አንዱ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ መሉ ተሳትፎ በሚያደርጉበት ጊዜ የተማሪዎች የውጤት ደረጃ ያድጋል የልጆቻቸው ከትምህርት ገበታ ላይ የመቅረት ሁኔታ ይሻሻላል። እንደዚሁም የቤት ሥራዎቻቸውን በወቅቱ እንዲሠሩ ከመርዳቱ ሌላ ለባህርያቸው መሻሻልም ትርጉም ያለው አስተዋፃኦ ይኖረዋል።

ስለትምህርት ያላቸው ዝንባሌም የበለጠ አዎንታዊ ይሆናል። ይህም በበኩሉ ተማሪዎች ሳያቋርጡ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ለከፍተኛ ውጤት እንዲበቁ ያስችላል።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ህፃናት በአካል፣ በአእምሮ፣በማኅበራዊና በስሜት ገና ያልዳበሩ በመሆናቸው ኃላፊነቱን ሙሉ ለሙሉ ለተቋማቱ ከመተው ይልቅ ወላጆች በተቋማቱ በመገኘት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል።

ሕፃናት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት መሳተፍ ለወደፊት ሕይታቸው መሠረት የሚጣልበት ሲሆን፣ ፕሮግራሙን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ወጪ መንግሥት ብቻውን ስለማይችል ወላጆች እነዚህን ተቋማት በገንዘብና በማቴሪያል በመደገፍ የሕፃናቱ የተሟላ አገልግሎት እንዲያገኙ ወላጆች የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

### 1.16.2 የአመራር ሚና

የትምህርት አመራርና አስተዳደር ባልተማከለ መንገድ የሚካሄድና የአካባቢውን ማኅበረሰብ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት አመራርና አስተዳደር የተቋማቱን፣ የወላጆችንና የአካባቢውን ማኅበረሰብ አባላት እና ባለድርሻዎች ያቀፈና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎን ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን ተሳትፏቸውን በሚከተሉት መድረኮች ሊገልጹ ይችላሉ።

- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ኮሚቴ ወይም ቦርድ ውስጥ ኅብረተሰቡን በመወከል
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም የወላጅ ኮሚቴ ውስጥ ወላጆችን በመወከል

### 1.16.3 የኅብረተሰብ ሚና

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋሙና የአካባቢው ማህበረሰብ ግንኙነት የተጠናከረ መሆን ይገባዋል።

የዚህም ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ምን እየሠራ እንዳለና የፕሮግራሙን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ሃሣብ ለማካፈል፣ ለምሳሌ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋሙ ኃላፊነቱን በብቃት እየተወጣ መሆኑንና ስለ ዓላማውና የዓላማውን ተግባራዊነት ለኅብረተሰቡ ማሳወቅ ከኅብረተሰቡ የሚሰጡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ የተቋሙን የሥራ አመራር ሥራውን እንዲያሻሽል ለማድረግ፣
- ሕፃናቱ በፕሮግራሙ ስላላቸው ተሳትፎና ውጤት ወላጆች አውቀው ተገቢውን ክትትል ለማድረግ፣
- የወላጆችንና የመምህራንን ግንኙነት ለማጠናከርና የፕሮግራሙ ውጤት ይበልጥ የተሻለ እንዲሆን ለማስቻል
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ኮሚቴ ወይም ቦርድ ውስጥ በመሳተፍ፣

ተቋሙን ለማጠናከር በሚቀርብ ዕቅድ ላይ ውይይት በማካሄድ መርምሮና አሻሽሎ ለማጽደቅ እና አፈጻጸሙንም ለመከታተልና ለመቆጣጠር፣

ሥርዓተ ትምህርቱ ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ተጣጥሞና ተዘምዶ ለሕፃናቱ መቅረቡን ለመከታተልና ሃሣብ ለመስጠት… ወዘተ ይሆናል።